# አፕሬሽን ሉቃስ

## መጠይቆች

### የግል ሁኔታን የሚመለከቱ

- ሙሉ ስምዎን? የት እንደሚኖሩ?
- ከመቼ ጀምሮ በጣልያን መኖር እንደ ጀመሩና መቼና የት ጌታን እንደ ግል አዳኝዎ እንደተቀበሉ? አሁን በየት ቤተክርስቲያን እንደታቀፉ? የሚያገለግሉ ከሆነ ያለዎት የአገልግሎት ስፍራና ሃላፊነት? በጣልያን ምድር ባሉ ሌሎች ከተሞች ተቀምጠዉ የሚያዉቁ ከሆነ የት? ከመቼ እስከ መቼ? እርስዎንና (የወከሉትን አጥቢያ ወይም ህብረት) ልናገኝበት የምንችልበት አድራሻ?
- ከስራችን ጋር ተያያዥነት ያለዉ ስለግል ህይወትዎ፣ ስላሉበት ከተማ ወይም ስለጣልያን የሚነግሩን የህይወት ምስክርነት ወይም ሊነግሩን የሚገባ ሌላ ተያያዥ ጉዳይ ካላ (እንዲህ አይነት የሰሩት ወይም የጀመሩት ተመሳሳይ ስራ ካለ፤ ስለጣልያን አብያተ ክርስቲያናት ከጌታ የተቀበሉት ልዩ ድምፅና ራዕይ ካለ፤ ወ.ዘ.ተ. )

### የአይን እማኝ የሆኑባቸዉ እዉነታወችን በተመለከተ

- ቤተክርስቲያኗን እንዴት፣ መቼና የት እንደ ጀመራችሁ? ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ነበረችዉ ቤተክርስቲያን (ህብረት) ሲሄዱ የተሰማዎት ስሜትና የነበረዉ ሁኔታ ምን ይመስል እንደነበር? የነበረዉ መንፈስ? የአመራር ቅርፁ? በወቅቱ የነበሩ አገልጋዮችና ምዕመናን እነማን እንደነበሩ? ጊዜና ዓመተ ምህረቱ? (የሚያስታዉሱ ከሆነ)
- በተግባር መሳተፍ ከጀመሩ በኋላ (በአጥቢያዉ ወይም በህብረቱ) ከሌሎች በተለየና በበለጠ መሰጠት ሲያገለግሉና ሲተጉ ያስተዋሏቸዉ፤ በታሪክ ተጠቃሽ ለመሆን የሚያበቃ ጉልህ ሚና የተጫወቱ ሰዎች ካሉ (በእርስዎ ሚዛንና ማስተያያ)
- ከዉጭ ሆነዉ ቤተክርስቲያኗን ወይም ህብረቱን ሲደግፍ ያዩት ግለሰብ ወይም ተቋም ካለ? (የዉጭ ዜጎች ግለሰቦችና አብያተ ክርስቲያናት፤ ማህበራዊና መንግስታዊ ተቋሞች፤ ወ.ዘ.ተ.)
- እነዚን ሁኔታወች የሚያስረግጡ ማስረጃወችና ፎቶወች በእጅዎ የሚገኙ ከሆነ (ገልብጠን ሶፍት ኮፒዉን በማስቀረት ልንመልስልዎ የምንችላቸዉ)

### *ሲባል ከሰሙትና ከተነገረዎት ተነስተዉ የሚሰጡን መረጃወች*

- እርስዎ ከመድረስዎ በፊት ስለነበረዉ የቤተክርስቲያኗ (የህብረቱ) ሁኔታ ሲባል የሰሙት ታሪክ ካለ? ወይም በሌሎች ሲባሉና ሲጠቀሱ የሰማችኋቸዉ ሰወች ካሉ?
- በጅማሬዉ ስራ ላይ ካዩትና ከሰሙት ተነስተዉ ለዚህ አጥቢያ (ህብረት) ከፍተኛ ዋጋ ከፍለዋል ሊረሱ አይገባቸዉም፤ ሊመሰገኑም ይገባቸዋል የሚሏቸዉ አገልጋዮችን ስም ቢጠቁሙን? (ይህም በእርስዎ ሚዛን)
- እነዚህ አገልጋዮች አሁን የት እንዳሉና በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ የሚያዉቁት ነገር ካለ? አድራሻቸዉና እነሱን ልናገኝበት የምንችልበት መንገድ ካለ? በጭምጭምታ ደረጃ የሰሟቸዉ ያልተጨበጡ መረጃወች ካሉ?
- በዚህ ከተማ ምን ያህል ቤተክርስቲያንና ህብረቶች አሉ? (ከአንድ በላይ ያሉባቸዉን ከተሞችን ብቻ የሚመለከት)
- እርስዎ ወንጌላዊያን አብያተ-ክርስቲያናት እንዳሉ የሰሙላቸዉ የጣልያን ከተሞች እነማን ናቸዉ? ህብረት እንዳለ የሰሙባቸዉ ከተሞችስ? ቅዱሳን እንዳሉ ግን ምንም እንደሌለ የሰሙባቸዉ ከተሞችስ?
- በእርስዎ የቆይታ ዘመን በዚህ ከተማም ሆነ አጠቃላይ በጣልያን አብያተ ክርስቲያናት ደረጃ በአንድ ወቅት የነበረና አሁን ተወስዶ ወይም ጠፍቶ ያዩት፤ እንዲመለስ የሚመኙት መንፈሳዊ ልማድ ወይም ነገር ካለ?
- ካለ . . . ለዚህ ነገር መታጣት ምክንያት ነዉ ብለዉ የሚያምኑት ነገር ምንድን ነዉ? (በእርስዎ እይታ)
- እንደዚሁ በእርስዎ ቆይታ ያልነበረ አሁን ግን እየመጣ ያለ እግዚአብሔርን የሚያመሰግኑበት መልክ ካለ?
- ካለ . . . ለዚህ ነገር መመለስ ምክንያት ይሆናል ብለዉ የሚያምኑበት መፍትሄ ምንድን ነዉ? (በእርስዎ እይታ)

- ከግል ግምገማዎ ተነስተዉ በወንጌላዊያን አብያተ ክርስቲያናት አሁን ስላለዉ አጠቃላይ (ከተማዊና አገር አቀፋዊ) መንፈሳዊ ይዘትና ህብረት  የሚሉት ነገር ካላ?

## *<u>ይህንን የኦፕሬሽን ሉቃስን ስራ በተመለከተ</u>*

- ይህ አይነት ስራና ራዕይ መሰራት መጀመሩን ሲሰሙ ምን ተሰማዎት? በዚህ ስራ ዉስጥ የእርስዎ ድርሻ ምን ድረስ እንዲሆን ይፈቅዳሉ?  (ይህ ስራ እንዳይስተጓጎል የሚኖሩ ማናቸዉንም ተግዳሮቶችን አብሮ ከማስወገድ አንፃር፤ ፅሁፉን በመገምገምና በማረም፤ በህትመት፤ በስርጭት፤ ወ.ዘ.ተ.)
- ለበለጠ ዉጤታማነት እንዴትና በምን ሁኔታ ቢሰራ ይሻላል ብለዉ የሚያዩት ሌላ ተጨማሪ መንገድ ካለ?
- ከዚህ ስራ አንፃር በእርስዎ በኩል ልናዉቃቸዉና ልንያያዛቸዉ የምንችላቸዉና ለስራዉ የሚያስፈልጉና የሚገቡ ሰወችና ተቋማት ካሉ ቢዘረዝሩልን? (ከእነዚህ እርስዎ ሊያገናኙን ፈቃደኛ የሆኑባቸዉ?)
- ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ ለምድሪቱ ቤተ ክርስቲያን ምን ያስገኛል ብለዉ ያስባሉ?
- በአለም አቀፍ ደረጃ ላለችዉ ለዲያስፖራዋ ቤተ ክርስቲያንና በአንድም በሌላም ምክንያት የጣልያን ምድርን ለቀዉ የመኖሪያ አድራሻቸዉን ለለወጡ ቅዱሳንስ?
- መረጃን በፅሁፍ ከማስተላለፍና ታሪክን ከማዉረስ አንፃር ለትዉልዳችን ቅዱሳን ሁላችን የሚመክሩትና የሚያሳስቡት ነገር ካላ?
- በተጨማሪ ሊሉ የሚፈልጉት ወይም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?
- ምስጋና በማቅረብ ቃለ ምልልሱን በባርኮት ፀሎት መዝጋት።

## *<u>ማሳሰቢያ</u>*

መልስዎን በፅሁፍ ወይም በድምፅ ተቀድተዉ በኤሌክትሮኒክስ አድራሻወቻችን ወይም በፖስታ ሳጥን ቁጥራችን በቀጥታ ሊልኩልን የሚችሉ ሲሆን፤ የኦፕሬሽን ሉቃስ የከተማ አስተባባሪወችን ወይም አብሮ ሰራተኞችን በቀጥታ ማግኘት የምትችሉ፤ በእነሱ አማካኝነት እንዲደርሰን ማድረግ ትችላላችሁ። የጊዜን ዉድነት አማክለዉ በዘመናችን የተዘረጉት መገናኛ መስመሮች ስራችንን ያቀላጥፉልናልና ይጠቀሙባቸዉ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

**P.O.Box:-** **Gospel Believers the Unique 7000 church Rome**
**C|O Pastor Abebe Retta**
**Via Gerace 5,  00182 Roma**

**E-mail:-** u7000rome@gmail.com ,  abeitaly@yahoo.com

**Dropbox:-** abeitaly@yahoo.com

**Skype:-** abeitaly

**Mobile or viber:-** 0039-3889010756,  0039-3203069883

**Web site:-** Gospel Believers the Unique 7000 church Rome